**CPS and Foster Care during the corona virus crisis in Amharic**

## የልጆች ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት መስሪያ ቤትና የልጆች አያያዝና ክብካቤ በኮሮና ቀውስ ወቅት

የኮሮና ቫይረስ በፈጠረው ቀውስ ምክንያት እቤት የሚዊውሉ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ደህንነታቸው ተጠብቆ መኖር ይችሉ ዘንድ ተጨማሪ ድጋፍ ያሻቸዋል። በህፃናት ክብካቤ ማእከላት ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦችም የልጆቻቸው ጉዳይ ያሳስባቸዋል። ይህ መረጃ በዚህ ወቅት መደረግ ስለሚገባው ነገር ለቤተሰቦች አንዳንድ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

በመጀመሪያ ስለስራ ማጣት፣ መኖሪያ ቤት፣ ምግብ፣ የልጆች አያያዝና ህክምና ጉዳይ መረጃ ለማግኘት እነዚህን ድህረገፆች ይመልከቱ። (https://vplc.org/learn/covid-19-civil-legal-response-in-virginia/)

•

(https://www.commonhelp.virginia.gov/።

## የህፃናት ጥበቃ አገልግሎት መስሪያ ቤትና ፍርድቤቶች

የህፃናት ጥበቃ አገልግሎት መስሪያቤት (CPS በአሁኑ ወቅት የቤተሰብ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም በህፃናት ላይ የሚፈፀምን በደልና ተገቢ ያልሆነ አያያዝ በሚመለከት ምርመራ በማድረግ ላይ ነው። ለድርጅቱ ሰራተኞች ወይም በቤት ውስጥ ላለ ሰው ጤና የሚያሰጋ ነገር ከሌለ በቀር ክትትሉና ምርመራው የሚከናወነው በአካል በመገኘት ይሆናል። የጤና ስጋት ካለ ግን ግምገማው ወይም ምርመራው በስልክ ወይም በርቀት ቪዲዮ ግንኙነት ይደረጋል።

በቨርጅንያ የሚገኙ ፍርድቤቶች ሁሉ ቢያንስ ከመጋቢት 16 እስከሚያዝያ 26 ቀን 2020 አመተምህረት ድረስ የሚሰሩት በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ውስጥ ነው። ችሎቶች የሚሰየሙት አስቸኳይና በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለመመልከት ብቻ ነው። ለሌሎች ጉዳዮች ግን ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠታቸውን ይቀጥላሉ።

በአስቸኳይ ጊዜ ትእዛዙ መሰረት የህፃናት ጥበቃ አገልግሎትና ህፃናት ክብካቤ ጉዳዮችን በሚመለከት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ባስቸኳይ ሊሰሙ የሚችሉ 2 ጉዳዮች አሉ። እነዚህም የደህንነት ጥበቃ ትእዛዝ (protective orderእና ልጅን የመያዝና የማሳደግ መብት ለመንጠቅ የሚሰጥ ትእዛዝ removal order)ናቸው።

አብዝሀኞቹ ፍርድቤቶች እነዚህን ጉዳዮች የሚሰሙት በስልክ ወይም በርቀት በሚደረግ የቪዲዮ ግንኙነት ነው። አንዳንድ ፍርድቤቶች ግን ባለጉዳዮች በአካል ፍርድቤ እንዲቀርቡ ሊያዙ ይችላሉ።

•

ፍርድቤት በግንባር መቅረብ የሚገባዎ ስለመሆኑ ወይም ጉዳዮን በቪዲዮ መከታተል ይችሉ እንደሆነ ለማጣራት የወጣት ታራሚዎችና ቤተሰብ ጉዳይ ፍርድቤት ይደውሉ።

1. **የደህንነት ጥበቃ ትእዛዞች Protective Orders)**

● ያካባቢው የህፃናት ጥበቃ አገልግሎት መስሪያ ቤት ወላጅ ወይም አሳዳጊው ለልጁ ጤና ወይም ደህንነት አደገኛ የሆነ ተግባር ይፈፅማሉ ብሎ ከጠረጠረ የልጅ ደህንነት ጥበቃ ትእዛዝ እንዲሰጥለት ለፍርድቤት ሊያመለክት ይችላል። እንዲሁም ወላጁ ወይም አሳዳጊው አንድ ነገር እንዲያደርጉ ወይም እንዳያደርጉ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

እንዲሁም አንድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ሌላው ወላጅ ወይም አሳዳጊ የልጁን ደህንነት የሚጎዳ ተግባር እየፈፀመ ነው የሚል ስጋት ካደረበት የልጅ ደህንነት ጥበቃ ትዝዛዝ እንዲሰጥ ማመልከት ይችላል። እንዲሁም አንድ ወላጅ አንድ የቤተሰ አባል በሌላኛው የቤተሰብ አባል የሀይል ተገባር የሚፈፅም ከሆነ የቤተሰብ ደህንነት ጥበቃ ትዝዛዝ እንዲሰጥ ሊያመለክት ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ ይህን ድህረገፅ ይመልከቱ። (https://vplc.org/wp-content/uploads/2020/04/Family-Law-COVID-19_3p_FINAL.pdf.)።

የልጅዎ ደህንነት አሳሳቢ ሆኖ ከታየዎ አንዳንድ ፍርድቤቶች አሁንም አጣዳፊ የሆኑ የልጅ አያያዝ አቤቱታዎችን ሊቀበሉ ወይም ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረን ትእዛዝ ሊያሻሽሉ ይችላሉ። ሌሎች ፍርድቤቶች ደግሞ የሚቀበሉት የደህንነት ትዝዛዝ ማመልከቻዎችን ብቻ ሊሆን ይችላል። እርስዎ ማድረግ ስለሚገባዎ ነገር ጉዳዩን የያዘውን የወጣት ታራሚዎችና ቤተሰብ ፍርድቤት ደውለው ይጠይቁ።

2. **ልጅን የመያጥ ወይም የማሳደግ መብትን ስለመነጠቅ (removal order)**

የህፃናት ጥበቃ አግልግሎት መስሪያ ቤት ለልጁ ደህንነት የሚያሰጋ ሁኔታ አለ በሚል ልጅዎትን የወሰደ እንደሆነ እርምጃውን በወሰደ በጥቂት ሰአታት ጊዜ ውስጥ ልጅን የመያዝ ወይም የማሳደግ መብት የመንጠቅ ጉዳይ በፍርድቤት እንዲታይ ማመልከት አለበት። ይህም ካልሆነ ልጁን ከመውሰዱ በፊት ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድቤት ታይቶ ትእዛዝ እንዲሰጥ ሊጠይቅ ይችላል። ልጁ ከወላጁ በአስቸኳይ እንዲወሰድ ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን ልጅን የመያዝ ወይም የማሳደግ መብትን የመነጠቅ ጊዚያዊ ትእዛዝ

ጉዳይ ላይ ክርክር መሰማት ይኖርበታል።

ፍርድቤቱ የህፃናት ጥበቃ አገልግሎት መስሪያቤቱ ልጁን እንዲወስድ የሚፈቅድ ከሆነ ለእርስዎ የግል ጠበቃ ማቆም ይኖርበታል። እንዲሁም ለልጁ ጥቅም የሚበጀውን አጥንቶ አስተያየት የሚያቀርብ ልዩ ጠበቃ መመደብ አለበት።

● ከቀጣዩ ቀነቀጠሮ በፊት ጠበቃዎ በስልክ ወይም በቪድዮ የርቀት ግንኙነት ያነጋግርዎታል። እንዲሁም የልጁ ልዩ ጠበቃ ከእርስዎ, ከልጁ፣ ከቤተሰብ አባላትና ሌሎችም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር መወያየት አለበት።

መንግስት በተቻለ መጠን ልጅዎ ከእርስዎ እንዳይለይ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ አለበት። ልጁንም ከወሰዱ በኋላም ቢሆን ከልጅዎ ጋር እንዲገናኙ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት። ይህም ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ መኖሪያ መፈለግን፣ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥን፣ ልጅ ለማሳደግ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠርንን፣ የወላጅነት ምክር ወይም ትምህርት አገልግሎት መስጠትንና እርስዎም ሆኑ ልጅዎ የሚያስፈልጋችሁን ሌላ ማንኛውንም ድጋፍ መስጠትን ያካተተ ሊሆን ይችላል።

## ባሳዳጊ ጥበቃ ስር እያሉ ስለሚካሄድ የፍርድ ቤት ክርክር

የልጅ አስተዳደግ ክትትልና ስለልጁ ዘላቂ የኑሮ ሁኔታን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎች እንደአስቸኳይ ጉዳዮች አይታዩም። ሆኖም በሁለተኛ ደረጃ ከሚታዩ ጉዳዮች ዝርዝር ይካተታሉ። አንዳንዶቹ ጉዳዮች አሁን ሊታዩ ይችላሉ። ቀሪዎቹ ግን ያስቸኳይ ጊዜው እስኪያልፍ ሊቆዩ ይችላሉ። እንዲያም ሆኖ ዳኞች እንደነገሩ ሁኔታ እያዩ ውሳኔ ሊሰጡ ይችላሉ። አብዝሃኞቹ የልጅ ማሳደጊያ ማእከላት ጉዳዮች የሚታዩት በስልክ ወይም በርቀት ቪዲዮ ይሆናል። ሆኖም አንዳንድ ፍርድቤቶች በግንባር ያስችላሉ።

ምናልባት ልጅዎ በህፃናት ማሳደጊያ ቆይቶ ወደቤት ለመመለስ በሂደት ላይ ከነበረ ልጅዎ ወደቤት መመለስ እንዲችል በመጠየቅ ለፍርድቤት እንዲያመለክትልዎ ጠበቃዎን መጠየቅ ይችላሉ።

## ስለህፃናት ማሳደጊያ፣ ስለጉብኝት, አገልግሎትና ኮቢድ19 ጉዳይ

አንዳንዶቹ ባቅራቢያዎ የሚገኙ ጉዳይ መስሪያቤት እንደወትሮው ስራቸውን እያካሄዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ሌሎች ቢሮዎች ግን ተመሳሳይ ስራዎችን የሚያከናውኑት በስልክ ወይም በርቀት ቪዲዮ ግንኙነት ሊሆን ይችላል.

ጉዳዮትን የሚከታተለው የማህበራዊ ሰራተኛ በማእከል የሚገኘውን ልጅዎን መጎብኘት እንዲችሉ ሊረዳዎት ይችላል። ልጁ በህክምና ወይም ተሃድሶ አገልግሎት ማእከል ቢገባም መጎብኘት ይቻላል።) ልጅዎ እህት ወንድሞቹን ወይም አያቶቹን የናፈቀ እንደሆነ በስልክ አነጋግሮ ወይም በቪዲዮ አይቶ ደህንነታቸውን ይረዳ ዘንድ ሁኔታዎች እንዲመቻቹለት የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛውን ማነጋገር ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎችም የማህበራዊ ሰራተኛው በአካል እንዲገናኙ ሊያመቻች ይችላል። ከተከለከሉ ጠበቃዎን ማነጋገር ይችላሉ።

● እንዲሁም ስራ ካቆሙና የመንግስት ድጋፍ ካስፈለገዎ ወይም ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት ከፈለጉ ጉዳዮትን የሚከታተለውን ሰራተኛ እንዲረዳዎት ይጠይቁ። በስራ ላይ በነበሩበት ወቅት ሌሎች ልጆች ከነበርዎትና ለነርሱ ከመንግስት ቀለብ ከፈለጉ ማመልከት ይችላሉ። እርስዎና ልጅዎ ከአስቸኳይ ጊዜው በፊት ያገኙ የነበረውን አገልግሎት

አሁንም ማግኘት ትችላላችሁ። በስልክ ወይም በርቀት ቪዲዮ አገልግሎቶችን ለማግኘት ከተቸገሩ, ጉዳዮትን የሚከታተልልዎን ሰራተኛ ያነጋግሩ።

**ድጋፍ ስለሚያገኙባቸው ቦታዎች**

ቀጥሎ የተመለከቱትን ድህረገፆች ቢጎበኙ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። የቨርጅንያ ድጋፍ አገልግሎት መጠየቂያ ማእከል

Virginia CommonHelp--apply for assistance: https://commonhelp.virginia.gov/

- ስለፍርድቤት መረጃ ለማግኘትይህን ድህረገፅ ይመልከቱ። : https://selfhelp.vacourts.gov/node/4/find-your-

- ስለልጆች ድጋፍ ወይም ቀለብ ጉዳይ: ይህን ይመልከቱ። https://mychildsupport.dss.virginia.gov/

ስለወላጆች ፋታና ክብካቤ ድጋፍ ስለማግኘት: ይህን ይመልከቱ።

የቤተዘመድ ክብካቤ አገልግሎት: ጉዳይ መረጃ ለማግኘት ይህን ይመልከቱ። lhttps://chsva.org/other-services/kinship-services/

ለልጅ ጥበቃ ድጋፍ: ጉዳይ ይህን ይመልከቱ። https://www.dss.virginia.gov/cc/covid-19docs/Virginia%20Child%20Care%20Subsidy%20Program%20COVID-19%20FAQ.pdf